አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ያወጣል።

9/ <u>የአፈጻጸም መመሪያ</u>

የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል።

10/ <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የውጭ ማስታወቂያ በሚጠቀም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

11/ <u>ቅጣት</u>

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ-መሠረት ይቀጣል።

12/ <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ኅዳር 14 ቀን 1991 ዓ.ም

ሐረር

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት